# ያኔ ይገባችኋል

ተፈጥሮ የቸራትን ፣ የፈጣሪን ስራ
በግራም በቀኝም ፣ አድርጋ አንሸዋራ
ያስተዳደር በደል ፣ አርጋ ስታወራ
የዋህ ሕዝብ አግኝታ ፣ ሆና ባለተራ
ስጋውን ጋግጣ ፣ መቅኒውን ሰርስራ
ሺዎችን አግዛ ፣ ወህኒ ቤት ጨምራ
አልያዝ ያላትን ፣ ከሃገር አባራ
ሕዝቡንም ምድሩንም ፣ በላቻቸው መትራ ፡፡

በሆነ አጋጣሚ ፣ የማታ የማታ
እድል ብትቸራት ፣ ድንገት እጇ ገብታ
ያልለመደባትን ፣ ተድላና ደስታ
ትላንት ተዘንግቷት ፣ ጠፍታ ከትዝታ
የደደቢት ደደብ ፣ በትዕቢት ተሞልታ
የማትጠግብ ሆነች ፣ አገር ግጣ በልታ
ካልሞተች በራሷ ፣ አቀርሽታ ተፍታ
መሞቻዋ ደርሷል ፣ ልትጣል ተገፍታ ፡፡

መፃጉ የእንግዴ ልጅ ፣ የባንዳዎች ድቃይ
በዘር በሃይማኖት ፣ ሕዝቦችን ከፋፋይ
የባዕድ ቅጥረኛ ፣ ገንጣይና አስገንጣይ
ሃጎስና ኀይቶም ፣ ብርክቲና ተክላይ
ዛሬ  እንዳሾፉበት ፣ በሕዝብ በሃገር ላይ
እንደ ሸክላ ፈርሰው ፣ ተሰባብረው ሳያይ
ወጣት ተማምሏል ፣ ወደኋላ ላያይ ፡፡

መቼ ተያዘና ፣ መቼ ተጀምሮ
ሺመልስ መገርሳ ፣ የነበረው ድሮ
በግደይ አስገዶም ፣ ሃጎስ ተቀይሮ
የወያኔን መንጋ ፣ ግልገሉን ጨምሮ
በገነባት ወህኒ ፣ ቂሊንጦ ታጉሮ
እንኳን ውስኪ ሊራጭ ፣ ሳያርበት ሽሮ
ሳያሰማ ጩኸት ፣ ዋይታንና እሮሮ
በትቢት ያበጠው ፣ ቅስሙ ተሰባብሮ
ባበጃት እስር ቤት ፣ ሳያለቅስ አምርሮ
የአማራው ወጣት ፣ የኦሮሞው ቄሮ
እንቅልፍም አይኖረው ፣ ወይ ፍንክች ዘንድሮ
ግባ መሬት ሳይል ፣ ወያኔ ተቀብሮ ፡፡

ከተከዜ ወዲያ ፣ ወንዙን ሲሻገሩ
ስንዴውና ጤፉ ፣ የህል አይነት ዘሩ
ሱሚ ነው ከእንግዲህ ፣ ብለው ሲዘምሩ
ቁልቋል ብቻ ሲሆን ፣ መስኩም ሆነ አጥሩ
ከበሮን መጠለዝ ፣ ውስኪን ማንቃረሩ
ሲዳሩ እየዋሉ ፣ ሲዳሩ ማደሩ
ጋለሞታን አቅፎ ፣ ማለት እሹሩሩ
ትላንትና ሆነው ፣ ዳግም ላይጠሩ
እንደልማዳችሁ ፣ ማከክ ስትጀምሩ
ያኔ ይገባችኋል ፣ ሁሉም እንደቀሩ ፡፡

ታዛቢው
January 10, 2018